በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የሜዲካል ኮሌጅን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት ይመለከታል፤

በርዕሱ የተጠቀሰውን ሜዲካል ኮሌጅ የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦችን የያዘ 24 ገጽ የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት (Final Management Letter) እና 9 ገጽ አባሪ በድምሩ 33 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከናል። በመሆኑም በገጽ 34 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር !

ሰለሞን መብራቱ

የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች

ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

ሚያዝያ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ

የዚህ ደብዳቤ ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን የሜዲካል ኮሌጁ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግሥት ኦዲት ደረጃዎችን (INTOSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን የሚያካትተው፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣

- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫዎቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡ አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ ግድፈቶችና ስህተቶች ሁሉ ሊታወቁ የሚችሉት ይህን አስመልክቶ ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ልዩ የዝርዝር ኦዲት በጥልቀት ሲከናወን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የሥራ አመራር በ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች ረቂቅ ሪፖርት ላይ ምላሽ እንዲሰጥ የካቲት 27 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር OFAG.F-02.19/2/12 በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት ሜዲካል ኮሌጁ መጋቢት 4 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር 1.2.8/123 በጻፈው ደብዳቤ ምላሽ ሰጥቷል። በመሆኑም ለሥራ አመራሩ የተዘጋጀው የመጨረሻው ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. ተሰብሳቢ ሂሳብ

1.1 በደንቡ መሰረት ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ፤

1.1.1 ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ፤ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። በመሆኑም ሜዲካል ኮሌጁ በደንቡና በመመሪያው መሰረት የፈጸመ መሆኑ ሲጣራ በተለያዩ የተሰብሳቢ የሂሳብ ኮዶች (መደቦች)፡-

1. ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 2,606,168.29፣
2. ከአሥር ዓመት በላይ የቆየ ብር 13,774.33፣

በድምሩ ብር 2,619,942.62 በደንቡ መሰረት ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 1 ተያይዟል)

1.1.2 ሥጋት

- ☞ በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ የመንግሥት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊባክን ይችላል።
- ☞ ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ማረጋገጥ አይቻልም።

1.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች እንዲሰበሰቡ፤ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ ይኖርበታል። እንዲሁም የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል።

1.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- በሂሳብ ወደብ 4201 የተመዘገቡ ሂሣቦችን ከእለት እለት ሰነዳቸውን እያጣራን እየወራረድን የምንገኝ ሲሆን፣ ቀሪውንም ለማጠቃለል አዳጋች የሆነብን ሰነዱ የቆየ ከመሆኑ የተነሳ የግለሰቦቹን ፋይል በቀላሉ ማግኘት ባለመቻሉ ነው። ይህም ሆኖ ግን አሁን የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እስከ 1998 ድረስ ያሉትን ሂሣቦች ውሳኔ ለማሰጠት እንዲቀርብ በታዘዘው መሰረት ለማቅረብ መረጃ እያሰባሰብን እንገኛለን።
- ከአንድ ወር እስከ አሥር አመት የቆዩት ሂሣቦች ለምርምር ስራ ተሰጥተው ያልተወራረዱ ሲሆኑ እየተከታተልን እንዲያወራርዱ እያደረግን እንገኛለን።

1.2 በተቀጽላ ሌጀሮች ላይ የተመለከተው የ2009 በጀት አመት የተሰብሳቢ ሂሳብ መነሻ (Opening Balance) ክሬዲት ሚዛን የሚያሳይ ስለመሆኑ፤

1.2.1 ግኝት

በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት ተሰብሳቢ ሒሳቦች የዴቢት መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከ2008 በጀት ዓመት ወደ 2009 በጀት ዓመት በተሰብሳቢ ተቀጽላ ለጀሮች ላይ የዞረው ከወጪ ቀሪ መነሻ ሚዛን (Beginning Balance) በ4211 የሂሳብ መደብ ብር 55,521.37 እና በ4253 የሂሳብ መደብ ብር 103,001.85 በድምሩ ብር 158,523.22 ክሬዲት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 2 ተያይዟል)

1.2.2 ሥጋት

ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ወይም የክሬዲት ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ከሆነ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ በየሒሳብ መደቡ የተመለከቱትን ሂሳቦች ትክለክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

1.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ወይም የክሬዲት ሚዛናቸውን የጠበቁ ለመሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል። የሂሳቡም ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል።

1.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በተቀጽላ ሌጀሮች ላይ የሚታየው ክሬዲት ሚዛን ወደ ኋላ በማጣራት በወሰዱት ገንዘብ እንዲወራረድ አድርገን አስተካክለናል።

1.2.5 የኦዲተሩ አስተያየት

1. በሂሳብ መደብ 4211 ለሰራተኞች ልዩ ልዩ ክፍያዎች ተፈጽመው ሂሳቡ ሲወራረድ በብልጫ ለሚያቀርቡት የወጪ ማስረጃ ገንዘቡ እንዲተካላቸው ሳይደረግ በወጪ መመዝገብ እና ያልወሰዱትን ተሰብሳቢ ሂሳብ በክሬዲት መመዝገብ ለልዩነቱ መፈጠር ምክንያት ስለሆነ ሁኔታው ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ መደረግ ይኖርበታል። ለወደፊቱም ተሰብሳቢ ሂሳቦች ሲወራረዱ በአመዘጋገብ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

2. ሒሳብ ከመዘጋቱ በፊትና ሂሳብ ከተዘጋ በኋላ የሚደረገው የሂሳብ ማስተካከያ ይለያያል። ይኸውም፡-

   ☞ ሒሳብ ሳይዘጋ በፊት በጊዜያዊ ሒሳቦች ላይ (በገቢና በወጪ) የሚደረገው የሂሳብ ማስተካከያ በዴቢትና በክሬዲት የተመዘገቡትን ሂሳቦች በመቀያየር (Reversing Entry) ማስተካከያ የሚሰራ ሲሆን፣ ሒሳብ ከተዘጋ በኋላ ደግሞ የተጣራ ሀብትን (Equity) ወይም ለዚሁ

ተብሎ በተዘጋጀ አካውንት መሠረት የሒሳብ ማስተካከያ መሠራት ይኖርበታል፡፡

☞ ቋሚ ሒሳቦች (ጥሬ ገንዘብ፣ ተሰብሳቢ፣ ተከፋይና የመሳሰሉት) የማይዘጉ በመሆኑ በነዚህ ሂሳቦች ላይ የሚደረገው የሒሳብ ማስተካከያ ሂሳቡ ቢዘጋም ባይዘጋም በዴቢትና በክሬዲት የተመዘገቡትን ሂሳቦች በማቀያየር (Reversing Entry) የሒሳብ ማስተካከያ መሠራት ይኖርበታል፡፡

ሆኖም በሜዲካል ኮሌጁ የተደረጉት የሂሳብ ማስተካከያዎች ሂሳቡ ከተዘጋ በኋላ የተደረጉ እና ለጊዜያዊ ሒሳቦች ከላይ በተራ ቁጥር 2.1 በተገለፀው መሠረት ሂሳቡ ሳይዘጋ በፊት ሊሰራ የሚገባው ማስተካከያ የተሰራ በመሆኑ አግባብነት የለውም፡፡ ስለሆነም የማስተካከያ ምዝገባው ተስተካክሎ እንዲሰራ መደረግ እንዳለበት እናሳስባለን፡፡

2. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

2.1 <u>ከመመሪያ ወጪ የተፈጸመ የውሎ አበል ክፍያ</u>፤

2.1.1 <u>ግኝት</u>

ከመደበኛ የሥራ ጊዜአቸው ውጪ በዘላቂነት አገልግሎት መስጠት በሚያስገድዱ የሾፌር መደቦች ላይ ተመድበው ለሚሰሩ ሰራተኞች ከየካቲት 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ልዩ አበል ስለመፈቀዱ ከሲቪል ሰርቪስ (ከፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር) ጥር 9 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ 30/ጠ/13/49/1056 እና ሚያዝያ 16 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ 30/ጠ/13/49/1062 በተጻፈ ደብዳቤ መመሪያ የተላለፈ ሲሆን፣ ጥር 19 ቀን 2008 ዓ.ም ደግሞ ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር በቁጥር ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ30/ጠ/13/46/1010 በተጻፈው ደብዳቤ መሰረት ደግሞ ከጥር 1 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ከክፍያው ላይ ግብር እንዲቀነስ ሆኖ አበሉ ቀጥሎ በተመለከተው መሰረት እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

1. በመንግሥት ለተሾሙ የበላይ ኃላፊዎች በዘላቂነት አገልግሎት ለሚሰጡ ሾፌሮች በወር ብር 800.00፤

2. በሥራ ባህሪያቸው ምክንያት ከመደበኛ የሥራ ሰዓት በፊት ወደ ሥራ ለሚገቡ እና አምሽተው ለሚወጡ ሰራተኞች የሚያገለግሉ የሰርቪስ ሾፌሮች ብር 600.00፤

3. ለሰራተኞች የሰርቪስ አገልግሎት በሚሰጡ አውቶብሶች ላይ በሾፌር ረዳትነት ተመድበው ለሚሰሩ በሥራ በህሪያቸው ምክንያት ከመደበኛ የሥራ ሰዓት በፊት ወደ ሥራ የሚገቡና የሚወጡ ሰራተኞችን ከሾፌሮች ጋር የሚያገለግሉ እና ከሾፌሮች እኩል በትርፍ ጊዜ በሥራ ላይ ለሚቆዩ ብር 400.00፤

እንዲከፈል የተፈቀደ እና በተለያዩ ተቋማት ይከፈሉ የነበሩ የተወሰኑ የሙያ አበል፣ የትርፍ ሰዓት አበል እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች ይህ መመሪያ ከወጣ ጀምሮ ተፈጻሚ እንዳይደረግ መመሪያው በግልጽ አስቀምጧል። ሆኖም የሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ሾፌሮች ቅዳሜ፣ እሁድ እና አምሽተው ለሰሩበት ተብሎ ከመመሪያ ወጪ አለአግባብ ብር 66,494.34 የውሎ አበል ክፍያ እንዲፈጸም የተደረገ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 3 ተያይዟል)

2.1.2 *ሥጋት*

- ☞ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- ☞ የወጣውን መመሪያ ተከትሎ ክፍያ ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያሥከትል ይችላል።

2.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

አለአግባብ ከመመሪያ ውጭ የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ እንዲሆን፣ ለወደፊቱም ለትርፍ ሰዓት ሥራ የሚፈጸሙ ክፍያዎች መመሪያውን ተከትለው እንዲፈጸሙ መደረግ ይኖርበታል።

2.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ከመመሪያ ውጪ የተፈጸመ የሹፌሮች የትርፍ ሰዓት ክፍያን በተሰጠው አስተየየትና በመመሪያው መሰረት አሰራሩን እናስተካክላለን። ገንዘቡንም ተመላሽ እናስደርጋለን። ይሁንና ግን ክፍያው ሲፈጸም የነበረው በዋንኛነት ለአምቡላንስ ሰራተኞች ሲሆን ይህ ስራ ደግሞ ጊዜና ሰዓት ስለማይገድበው

ነው። በመሆኑም ወደፊት አመራርና ፍቃድ የምንጠይቅበት ሆኖ በአሁኑ ወቅት ግን በተሰጠው አስተያየት መሰረት ማስተካከያ እናደርጋለን።

2.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ሜዲካል ኮሌጁ በወጣው መመሪያ መሰረት አሰራሩን ማስተካከል ይኖርበታል። ለሾፌሮች በልዩ ሁኔታ አበል የተፈቀደው የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዲቆም ለማድረግ ተብሎ እንደሆነ በመመሪያው ላይ በግልጽ ተመልክቷል። ይህ ካልሆነ ግን ሜዲካል ኮሌጁ የሚመለከተውን የመንግሥት አካል ማስፈቀድ ይኖርበታል።

2.2 <u>ሳይፈቀድ የተፈጸመ የትራንስፖርት አበል ክፍያ</u>፤

2.2.1 <u>ግኝት</u>

ጥቅምት 14 ቀን 1970 ዓ.ም በወጣው የመንግሥት ሠራተኞች የልዩ ልዩ አበሎች ክፍያ መመሪያ ቁጥር 1/መ58/31 መሠረት የትራንስፖርት አበል የሚከፈለው አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በከተማ ክልል ውስጥ ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ አዘወትሮ እየተዘዋወረ ለሚያከናውነው ሥራ ማስፈጸሚያ እንደሆነና ለሥራ መደቡ ሲፈቀድ ተግባራዊ እንደሚደረግ ተመልክቷል። ሆኖም ሜዲካል ኮሌጁ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴርን ሳያስፈቅድ አቶ አይናለም አሸብር ለተባሉ የኮሌጁ ፖስተኛ ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ በወር ብር 500.00 የ10 ወር በድምሩ ብር 5,000.00 ለትራንስፖርት በሚል ክፍያ ፈፅሞ ተገኝቷል።

2.2.2 <u>ሥጋት</u>

በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ ክፍያ መፈጸም ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል።

2.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ሳይፈቀድ የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነቱ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ሚኒስቴር እንዲፈቀድ መደረግ ይኖርበታል።

2.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ሳይፈቀድ የተፈጸመ የትራንስፖርት አበል ክፍያ ከጥቅምት ወር 2010 ዓ.ም ጀምሮ እንዲቋረጥ ያደረግን ሲሆን አላግባብ የተፈጸመውን ክፍያም ተመላሽ እንዲያደርጉ ደብዳቤ ተጽፎ ተመላሽ አያደረጉ ይገኛሉ። ወደፊትም ሙሉ በሙሉ ተመላሽ በማድረግ ሪፖርት የምናደርግ መሆናችንን እንገልጻለን።

2.3 ከመመሪያ ውጭ የተፈጸመ የቤት ኪራይ ክፍያ፤

2.3.1 ግኝት

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ሰኔ 17 ቀን 2005 በቁጥር መ200-8/3/6 በተጻፈ ደብዳቤ ለጤና ሙያተኞች ከፈቀደው የተሻሻለ የተረኝነት አበል እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ውስጥ አንዱ ለመኖሪያ ቤት ኪራይ ማካካሻ የሚሆን እንደ ኃላፊነታቸው የሚከፈል የቤት አበል መሆኑ ይታወቃል። ይሁንና ሜዲካል ኮሌጁ መመሪያውን ባልተከተለ ሁኔታ ለሶስት የአቤት ሆስፒታል ዶክተሮች እና አንደኛው የመኖሪያ ቤት ኪራይ ለምን አገልግሎት እንደተፈጸመ የማይታወቅ ሲሆን ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት የሚደርስ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ውል በየወሩ ብር 10,000.00 ፈጽሞ ከሶስት ወር አስከ አንድ ዓመት ለሚደርስ ጊዜ በጠቅላላው በብር 270,000.00 የመኖሪያ ቤት የቅድሚያ ኪራይ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል። (ዝርዝሩ አባሪ 4 ተያይዟል)

2.3.2 ሥጋት

- ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ እንዲወጣ ምክንት ሊሆን ይችላል።
- ከወጣው መመሪያ ወጪ ክፍያ መፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።

2.3.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ኮሌጁ የወጣውን መመሪያ ሳይከተል የፈጸመው ክፍያ በአስቸኳይ እንዲቆምና በመመሪያው መሰረት እንዲፈጸም። ወይም ኮሌጁ የሚመለከተውን አካል ማስፈቀድ ይኖርበታል።

2.3.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ኮሌጁ በቅርቡ ለከፈተው የድንገተኛና የቃጠሎ ሆስፒታል በከተማዋና በዙሪያዋ ለሚደርሱ የተለያዩ አደጋዎች የሕክምና አገልግሎቱ፣ የአስክሬን ምርመራና የሰነ-ምርዛ ህክምና የሚሰጥ ሲሆን ይህም ሆስፒታል አገልግሎቱን የተሻለ ለማድረግ እና በዚህ ዙሪያ ያሉ ባለሙያዎች በአገር ደረጃ እጅግ በጣም አነስተኛ በመሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ ሙያው በአገር ደረጃ እጅግ ተፈላጊ በመሆኑ እና በአገር ደረጃ እጥረት ለሚታይባቸው የጤና ባለሙያዎች መንግሥት ቤት እየሰጠ በመሆኑ ለባለሙያዎቹ ቤት መስጠት እንደ አንድ አማራጭ ተወስዶ በወቅቱ ኮሌጁ ያሉት ውስን ቤቶች የተያዙ በመሆናቸው የተፈጸመ ነው። ሆኖም ግን ኮሌጁ ችግሩን በዘላቂነት መፍታት እስከሚቻል ድረስ ኪራዩ ቀጣይ በመሆኑ ለመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ህዳር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር 1.55/6 በተጻፈ ደብዳቤ ጉዳዩን ጠቅሰን ቤት እንድንከራይ እንዲፈቀድልን ጠይቀን ኤጀንሲውም ህዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር መግኤ/ጠ-4/1/1590 በጻፈው ደብዳቤ መሰረት በሰጠን ልዩ ፈቃድ መሰረት እየሰራን እንገኛለን።

2.3.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

1. ሜዲካል ኮሌጁ በ2010 በጀት ዓመት ግዥ ኤጀንሲን የተጠየቀበትና ምላሽ የሰጠበት ደብዳቤ በ2009 በጀት ዓመት ለተፈጸመው ክፍያ እንደማስረጃ ሊቀርብ አይገባም።
2. ኮሌጁ የቤት ኪራይ አገልግሎት ግዥውን ለመፈጸም እንዲችል የግዥ ኤጀንሲ በጻፈው ደብዳቤ ላይ በገለጸው አግባብ መፈጸም እንዲችል በልዩ ሁኔታ ፈቅዷል። ሆኖም ግዥው በልዩ ሁኔታ ተፈቀደ ማለት ለሐኪሞች የመኖሪያ ቤት ተከራይታችሁ ስጡ ማለት እንዳልሆነ እና በቅድሚያ

ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጋር መመካከር እንዳለባችሁ የተገለጸና ይህ ለመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበ ሲሆን መኖሪያ ቤት ለሐኪሞች እንድትከራዩ ፍቃድ መስጠት የኤጀንሲው ተግባርና ኃላፊነት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል። ሆኖም ሜዲካል ኮሌጁ በሚመለከተው የመንግሥት አካል ሳይፈቀድ የቤት ኪራይ ክፍያ መፈጸሙ አግባብ ካለመሆኑም በተጨማሪ በጀቱን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት ለመደገፍና በጀትን በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻል የሚያደርገው ከመሆኑም በተጨማሪ የቤት ኪራዩ በሚመለከተው የመንግሥት አካል ሳይፈቀድ የተፈጸመው አሰራር ተቀባይነት አይኖረውም። ስለሆነም የቤት ኪራይ ክፍያው በአስቸኳይ እንዲቆም እናሳስባለን።

2.4 <u>ጨረታ ሳይወጣ በቀጥታ የተፈጸመ የአገልግሎት ግዥ</u>፤

2.4.1 <u>ግኝት</u>

ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 በወጣው መመሪያ መሰረት ከብር 150,000.00 በላይ ለሚፈጸሙ የአገልግሎት ግዥዎች ጨረታ መውጣቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሜዲካል ኮሌጁ የካቲት 30 ቀን 2006 ዓ.ም ከህንጻ ዲዛይን አክሲዮን ማኅበር ጋር የአፈር ምርመራ ውል ሥምምነት የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ በብር 693,910.00 ተፈርሞ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ብር 674,388.75 ክፍያ የፈጸመ መሆኑ ታውቋል።

2.4.2 <u>ሥጋት</u>

☞ በግዢ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፤ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል ያደርጋል።

☞ የመንግሥት ግዢ አፈጻጸምን ቀልጣፈና ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት መደገፍ እንዳይቻልና በጀትን በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻል ያደርጋል።

☞ ግልጽ አሰራር እንዳይኖር እና የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

☞ የግዥ አዋጁን እና መመሪያውን ተከትሎ ግዥዎችን ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል። በደመወዝ አከፋፈል ወቅት ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ካልተደረገ የመንግሥት ገንዘብ ያላግባብ ሊባክን ይችላል።

2.4.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ኮሌጁ የሚፈጽማቸውን ግዥዎች በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል።

2.4.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ኮሌጃችን ከኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ ኢንስቲትዩት ጋር በነበረው ለግንባታ የሚሆን በመሬት መጋራት ሂደት ላይ ሃሳቦች እየቀረቡ ለዓመታት ሳይሳካ ከቆየ በኋላ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤታችን አደራዳሪነት ጉዳዩ ሲቋጭ የአማካሪና ሌሎች ተዛማጆች ቅጥር ተካሂዶ ስለነበረና በሀገራችን ያለውን የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት እንዲገነቡ በዕቅድ ከተያዙት 6 ትላልቅ የካንሠር ማዕከላት ውስጥ አምስቱ ቀድመው የተጀመሩ መሆናቸውና በኮሌጃችን ሥር የሚገነባው አገራዊ የካንሠርና የልብ ማዕከል ግንባታ ከላይ በተጠቀሰው የመሬት መጋራት ምክንያት ወደ ኋላ ቀርቶ ስለነበር ለአፈር ምርመራው ግልጽ ጨረታ ቢወጣ ሊጠፋ የሚችለውን ጊዜ ለመቆጠብ ሲባል ይህን አገልግሎት ከሚሰጠው ብቸኛ የመንግሥት የልማት ድርጅት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የህንጻና ከተማ ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ዘርፍ አገልግሎቱን እንዲሰጠን በጠየቅነው መሰረት የተሰራ ሲሆን ደርጅቱም የመንግሥት ተቋም ለመሆኑ ማረጋገጫ እንዲሰጠን ጠይቀን የላከልንን በመረጃነት አያይዘን

ያቀረብን ሲሆን ጨረታ ሳይወጣ በቀጥታ የአገልግሎት ግዥው ሊፈጸም የቻለ ሲሆን ለቀጣይ ግን በተሰጠን የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት እንሰራለን፡፡

2.4.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 3 ተራ ቁጥር 2"ለ" ላይ የተገለጸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን፣ የምክርና ሌሎች አግልግሎቶችን ወጪ በመሸፈን ከሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለማግኘት በሚያደርጉት ውል ላይ ይህ የግዥ አዋጁ ተፈጻሚ እንደማይሆን ተመልክቷል፡፡ በዚሁ የግዥ አዋጅ በትርጓሜ ሥር የመንግሥት መሥሪያ ቤት ማለት መሉ በሙሉ ወይም በከፊል በፌዴራል በመንግሥት በጀት የሚተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋምና ተመሳሳይ አቋም ያለው ለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ሥራዎች ኮርፖሬሽን አትራፊ ድርጅት እንጂ በበጀት የሚተዳደር አካል አይደለም፡፡ ስለሆነም ሜዲካል ኮሌጁ ለወደፊቱ ግዥዎችን መመሪያውን ተከትሎ መፈጸም እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

2.5 <u>በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያልተደረጉ የቋሚ ዕቃዎች ግዥ</u>፤

2.5.1 <u>ግኝት</u>

ኮሌጁ ህዳር 2 ቀን 2009 ዓ.ም በቁጥር 1.2/62 ለግዥ ኤጀንሲ በጻፈው ደብዳቤ የሕትመት ማሽንና ዲጂታል ፍሌክስ ባነር፣ ለልብ የህክምና አገልግሎት የሚውሉ ተያያዥ የህክምና ዘመናዊ ማሽኖች፣ የአጥንት ህክምና መሳሪዎችና ፈርኒቸሮች ግዥን የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ጨረታ አውጥቶ አሸናፊ አድርጓቸው ከነበሩት ድርጅቶች በቀጥታ መፈጸም እንዲችል እንዲፈቀድለት በጠየቀው መሰረት የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ታህሳስ 14 ቀን 2009 ዓ.ም በቁጥር መገኤ/ጡሃ/2/1225 በጻፈው ደብዳቤ ኮሌጁ የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ጨረታ አውጥቶ አሸናፊ አድርጓቸው ከነበሩት ድርጅቶች ባቀረቡት የነጠላ ዋጋ ላይ ምንም ለውጥ

ሳያደርግ ግዥውን በቀጥታ እንዲፈጸም ፈቅዷል። በዚሁ መሰረት የፈርኒቸር ግዥዎች በብር 23,285,506.72 ከሶስት ድርጅቶች ተፈጽሟል። ሆኖም ከተገዙት የተለያዩ የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች ውስጥ በብር 20,674,254.00 የተገዙት ቋሚ እቃዎቹ በሙሉ በጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊው ከንብረት ክፍል ወጪ ተደርገው፡-

1. 35 ጠረጴዛዎችና 1 ባለ ሶስት ተከፋች የፋይል ማስቀመጫ ቁም ሳጥን አዲሱ ህንጻ ምድር ቤት ውስጥ ኮሪደር ላይ በአዋራ ተሸፍነው የሚገኙ መሆኑ፣
2. በአዲሱ ህንጻ ምድር ቤት በስድሰት ቢሮዎችና በአካዳሚ ህንጻ ባለው አንድ ቢሮና ኮንቴነር ውስጥ ሶፋዎች፣ ጠረጴዛዎች፣ የኃላፊ ወንበሮች እንዲሁም የተለያዩ ቋሚ ዕቃዎች ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ ተደራርበው የሚገኙ መሆኑ፣
3. በአዲሱ ህንጻ በሁለት ቢሮዎች እና በአስተዳደር ህንጻ የቀድሞ ምግብ ማብሰያ ውስጥ ሶስት በአንድ የእንግዳ ወንበር የሚገኝ መሆኑ፣
4. በአዲሱ ህንጻ መውጫ በር ላይ አራት የንግዳ ወንበር ባለመደገፊያ ወድቆ የተገኘ መሆኑ፣

ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 5 ተያይዟል)

2.5.2. <u>ሥጋት</u>

- ☞ ግዥው ቁጠባንና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሚታን ያልገናዘበ ሊሆን ይችላል።
- ☞ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት እና ንብረት ለጥፋት ይዳረጋል።
- ☞ በንብረት ላይ አላስፈላጊ ክምችት ሊፈጠር ይችላል።
- ☞ ንብረቶች በወቅቱ አገልግሎት ለሚሰጡበት ክፍል መሰራጨት ካልቻሉ ለከፋ ብልሽት ሊዳረጉና ዋጋቸ ሊቀንስ እንዲሁም የመንግሥት ገንዘብ ሊባክን ይችላል።
- ☞ ለንብረት ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

2.5.3. የማሻሻያ ሃሳብ

የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲፈጸም እንዲሁም ኮሌጁ የቋሚ ዕቃ ግዥ ከመፈጸሙ በፊት የግዥ ፍላጎት (ጥያቄ) እንዲቀርብ መደረግ ይኖርበታል። ከዚህም በተጨማሪ የተያዘው በጀት ፈሰስ ይሆናል ተብሎ ተገንብቶ ላላለቀ ህንጻ ግዥ መፈጸም ተገቢ ስላልሆነ እንደዚህ ዓይነት አሰራር እንዲታረም መደረግ ይኖርበታል።

2.5.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ኮሌጁ በአሁኑ ወቅት እየተገነባ ባለው የእናቶችና ህጻናት ሆስፒታል ውስጥ የተለያዩ አዳዲስ የህክምና አይነቶች እየከፈተ እየተስፋፋ የሚገኝ በመሆኑ ዕቃዎቹ ለዚያ አገልግሎት እየዋሉ እየተሰራባቸው ይገኛሉ። ሆኖም በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት እናስተካክላለን።

2.5.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ለግዥው ዕቅድ የቀረበ ቢሆንም ግዥው ቁጠባንና ኢኮኖሚያው ጠቀሜታውን በማገናዘብ የተፈጸመ ባለመሆኑ የመንግሥት ገንዘብን ለብክነት፣ ለአላስፈላጊ የንብረት ክምችት መፍጠር ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ ተደራርበው የሚገኙ ዕቃዎች ለብልሽት እየተዳረጉ በመሆኑ ኮሌጁ በአስቸኳይ ተገቢ የሆነ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

2.6. በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፤

2.6.1. ግኝት

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለውጭ አገር ሥልጠና የተፈጸመው የውሎ አበል ክፍያ ብር 1,209,701.92 በሂሳብ መደብ 6272 መመዝገብ ሲገባው በ6231 የሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ተገኝቷል። (ለዝርዝሩ አባሪ 6 ተያይዟል)

2.6.2. ***ሥጋት***

☞ ወጪው በተገቢው ሂሳብ መደብ ካልተመዘገበ በየሂሳብ መደቡ የተመለከተው ሒሳብ ትክክለኛውን ከወጪ ቀሪ እንዳያሳይ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

☞ የሂሳብ መግለጫውን ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ ሊሆን ይችላል፡፡

2.6.3. ***የማሻሻያ ሃሳብ***

ወጪዎች የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት በተገቢው የሂሳብ መደብ እንዲመዘገቡ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለሂሳቡም ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.6.4. ***የሥራ አመራሩ ምላሽ***

እንደሚታወቀው ኮሌጁ የሚሰጠው የሕክምና፣ የትምህርትና የሥልጠና አገልግሎት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በሕክምናው እና መማር ማስተማሩ ላይ የተመደቡ ባለሙያዎች በኮሌጁ አማካኝነት ለአጭርና ረጅም ጊዜ ያሉትን ባለሙያዋች ወደ ውጪ አገር ልኮ የሚያስለጥንና የልምድ ልውውጥ አድርገው እንዲመጡ እንደሚልክ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጉዞ የሚውልው ክፍያ በሂሣብ መደብ 6231 ሊመዘገብ የቻለበት ዋናው ምክንያት በሚሄዱበት ሀገር ያለውን የውጪ ሀገር ጉዞ አበል ተመን መሰረት በመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ግን በተሰጠን የማሻሻያ ሃሣብ መሰረት እንዲሁም ከሚመለከተው አካል ጋር ተነጋግረን እና በተመሳሳይ ሥራ እና ተልዕኮ የተሰማሩት የሚሰሩበትን እና የበጀት አጠቃቀማችንን በትክክል ሊያሳይ በሚችል መልኩ እናስተካክላለን፡፡

2.6.5. ***የኦዲተሩ አስተያየት***

ኮሌጁ የህክምና አገልግሎቱን በተገቢው ሁኔታ ለማከናወን ይችል ዘንድ ባለሙያዎችን ማሰልጠኑ ተገቢነት እንዳለው ይታመናል፡፡ ሆኖም ኮሌጁ

የገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለውጭ ሥልጠና ክፍያ የሚሆን በጀት በተገቢው የሂሳብ መደብ (ኮድ) አስቀድሞ እንዲያዝ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም ባልተፈቀደ የሂሳብ መደብ (ኮድ) ክፍያ መፈጸም ተገቢነት የሌለው ስለሆነ አሰራሩ እንዲስተካከል መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.7. <u>በግዥ መመሪያ መሰረት ያልተፈጸመ የግንባታ ክፍያ</u>፤

2.7.1. <u>ግኝት</u>

ኮሌጁ ከኮንስትራክሽን ድርጅቶች ጋር ባደረገው የህንጻ ግንባታና የዕድሳት ውል መሰረት የተፈጸሙ ክፍያዎች በውሉና በህጉ መሰረት የተፈጸሙ እንዲሁም የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም. ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያን ተከትለው የተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ናእዳ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ በብር 1,955,807.60 የኦፕሬሽን ክፍል እና የኢንዶስኮፒ ህክምና ክፍል ጥገና ሥራ ለማከናወን ውል ፈጽሟል፡፡ በተጨማሪም ኮሌጁ የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ የብር 5,843,954.05 የተጨማሪ ሥራ ውል የተፈራረመ መሆኑ ታውቋል፡፡ ሆኖም በግዥ መመሪያው አንቀጽ 25(3ለ) መሰረት በተጨማሪነት የሚታዘዘው የግንባታ ሥራ የገንዘብ መጠን ከመጀመሪያው ውል ጠቅላላ ዋጋ ከ30% (ሰላሳ በመቶ) የበለጠ መሆን እንደሌለበት የተመለከተ ቢሆንም ለተጨማሪ ሥራዎች ተብሎ የተፈጸመው ውል ከመጀሪያው ውል ጋር ሲነጻጸር በ299% የጨመረ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.7.2. <u>ሥጋት</u>

በግዥ መመሪያው ከተፈቀደው በላይ ለለውጥ ሥራዎች ውል መፈጸም፡-

- ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

2.7.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ለለውጥ ሥራዎች ተብሎ ውል መፈጸም ያለበት የግዥ መመሪያውን ተከትሎ መሆን እንዳለበት ቀደም ሲል በተደረጉ የኦዲት ሥራ ወቅት በተደጋጋሚ የተገለጸ ቢሆንም በዚህ ኦዲት ወቅትም የግዥ መመሪያውን ሳይከተል ለተጨማሪ ሥራ በሚል ክፍያ መፈጸሙ ተገቢነት የለውም፡፡ ስለሆነም እንዲህ ዓይነቱ አሰራር ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑ ታውቆ አሰራር የግዥ መመሪያው በሚፈቅደው አግባብ መፈጸም እንዳለበት በድጋሚ ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

2.7.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ከውል በላይ ለተሰራው የግንባታ ክፍያ ዋናዎቹ ምክንያቶች በምላሽ ላይ የተጠቀሱት ሆነው ስለሌሎቹ ተቋራጭች ተጨማሪ ሥራ ከዚህ ቀደም በነበሩ ኦዲቶች የተሰጠውን አስተያየት ሳንቀበል በድጋሚ የተፈጸመ ሳይሆን በተመሳሳይ ጊዜ የተጨማሪ ሥራውና የልዩነት ሥራው ቀድሞ የተሰጠው ነው፡፡ የመጨረሻ ክፍያው ግን ዘግይቶ 2009 ላይ በመፈጸሙ የተከሰተ ነው፡፡ በሌሎች ኦዲቶች ወቅት ስለተጨማሪ ሥራ አስተያየት ያልተሰጠው ከውል በላይ ያለው ክፍያ የተፈጸመው በ2009 በጀት በመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም በተሰጠን የማሻሻያ ሃሣብ መሰረት እናስተካክላለን፡፡

2.7.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ሥራዎች መፈጸም ያለባቸው አዋጁና መመሪያው በሚፈቅደው አግባብ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለሆነም ሜዲካል ኮሌጁ የግዥ መመሪያውን ተከትሎ መፈጸም እንዳለበት በድጋሚ ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

3. ንብረት

3.1. በመድኃኒትና በህክምና ዕቃዎች ክፍል የንብረት አያያዝ ላይ የታዩ ክፍተቶች፤

3.1.1. ግኝት

የሜዲካል ኮሌጁ የመድኃኒትና የህክምና ዕቃዎች ክፍል የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአላቂና ቋሚ የህክምና ዕቃዎች አቅርቦት እና የመድኃኒት ግምጃ ቤት ቀጥሎ የተመለከቱት የአሰራር ክፍተቶች ታይተዋል። ይኸውም፡-

1. በመደበኛ መድኃኒት እቃ ግምጃ 23 ኢንዶስኮፒ፣ 57 ከአንገት በላይ የህክምና መሳሪያዎች ገቢ ሳይደረጉ እና 2 የፓቶሎጂ ማሽኖች አገልግሎት ሳይሰጡ በአዲሱ ህንጻ ምድር ቤት ወለል አዋራ ለብሰውና ሕንጻውን የሚሰሩ ሰራተኞች መረማመጃ እና መቆሚያ በመሆኑ ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣
3. በመደበኛ መድኃኒት እቃ ግምጃ በርካታ አገልግሎት የማይሰጡ የህክምና ቋሚ ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፣
4. በልዩ ፋርማሲ እስቶክ ካርድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
5. በርካታ ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች የሚገኙ መሆኑ፣

ታውቋል። በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም በአብዛኛዎቹ ላይ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም።

3.1.2. ሥጋት

☞ አሰራሩ በዚሁ ከቀጠለ የመንግሥት ንብረቶች ለብክነትና ለብልሽት ሊጋለጡ ይችላሉ።

☞ ለንብረት ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

3.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝ፣ አጠባበቅ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ መመሪያ መሠረት እንዲስተካከል እና እንዲፈፀም መደረግ ይኖርበታል።

3.1.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

1. ለመደበኛው መድኃኒት ዕቃ ግምጃ ቤት ዕቃዎች ገቢ ያልተደረጉበት ምክንያት አስመጭው ድርጅት ሁሉንም 'Spare Parts' ሙሉ በሙሉ ወደ ሀገር ውስጥ አስገብቶ ያልጨረሰ በመሆኑ ሲሆን የመረካከብ እና ገቢ ወጭ የማድረግ ሥራው የሚከናወነው ሁሉንም 'Spare Parts' ቀርበው በባለሙያ ተገጥመው መስራታቸው ሲረጋገጥ መሆኑን እየገለጽን አሁኑ ያሉት ወደ ሀገር ሲገቡ በመንገድ ላይ በቀላሉ እንዳይጎዱ በማሰብ ከነታሸጉበት ፓሌት ሳይፈቱ በአደራ መልክ የተቀመጡ ሲሆን ካለብን ከፍተኛ የማከማቻ (ግምጃ ቤት) ጥበት አንጻር በሌላ ቦታ ማስቀመጥ አለመቻላችንን እንገልጻለን።
2. አገልግሎት የማይሰጡ የህክምና ቋሚ ዕቃዎች በአመታዊ ቆጠራ በዝርዝር በመለየት ለጤና ጣቢያዎች፣ ለመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ለአገልግሎት እንዲሁም ለዩኒቨርስቲዎች ለማስተማሪያነት አገልግሎት የሚሰጡ በመሆናቸው በኢሜይልና በደብዳቤ በማሳወቅ ወደ አገልግሎት የሚገቡበትን መንገድ እየፈለግን ሲሆን ጥረታችንን አጠናክረን በመቀጠል ለክልል ጤና ቢሮዎችም ጭምር በማሳወቅ የማሰራጨት ስራ የምንሰራ መሆኑን እንገልጻለን።
3. በልዩ ፋርማሲ ስቶክ ካርድ አስከአሁን ያልነበረ መሆኑ ስህተታችን መሆኑ ተቀብለን በ2 ሳምንት ጊዜ ውስጥ ስራውን የምንጀምር መሆኑን እናሳውቃለን።
4. በኮሌጃችና የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸውን መድኃኒቶች በየወሩ ሪፖርት የምናዘጋጅ ሲሆን ባለፉት 4 ወራት (በአዲሱ በጀት ዓመት) በፐርሰንት ከ1% በታች ሲሆኑ (0.06, 0.1, 0.6) እንደአገር ከተያዘው ከ2%

በታች የማድረግ ዕቅድ አንጻር በጥሩ ሁኔታ ያለ ሲሆን፣ የተጠራቀሙትን በሥራ አመራር ውሳኔ የማስወገድ ስራ የዝግጅት ጊዜያችንን የጨረሰን ቢሆንም እንደአገር ካለው የማስወገጃ ቦታ ችግር ምክንያት ለማስቀመጥ ተገደናል። ይህንን ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ለምግብ፣ የመድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለሥልጣን፣ ለመድሃኒት ፈንድ እና አቅርቦት ኤጀንሲ የማስወገጃ ቦታ በማግኘት በኩል ድጋፍ እንዲያደረጉልና ብንጠይቅም እስከአሁን መፍትሔ አላገኘንም። ከባለድርሻ አካላት ጋር የምናደርገውን ውይይት አስፍተን ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ እንዲሁም ከአጎራባች ከተሞች (አዳማ፣ ደብረብርሃን) ከተማ መስተዳድሮች ጋር በመነጋገር የማስወገጃ ቦታ ፈቃድ ለማግኘት በኮሌጃችና አመራሮች በኩል ጥረት እያደረግን ሲሆን በተቻለ ፍጥነት የምናሰወግድ መሆኑን እንገልጻለን።

4. <u>በጀት</u>

4.1. <u>ከ10% በላይ ያልተሰራበት በጀትና ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ ሂሳብ</u>፤

4.1.1. <u>ግኝት</u>

ለኮሌጁ በ2009 በጀት ዓመት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው የወጪ በጀት አጠቃቀም ሲታይ፡-

- ✓ ከመደበኛ በጀት ከየሂሳብ ኮዶቹ ከ10% በላይ ብር 3,653,755.82 ሥራ ላይ ያልዋለ ሲሆን፣ ብር 1,544,097.92 ደግሞ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ መሆኑ፤
- ✓ ከካፒታል በጀት ከየሂሳብ ኮዶቹ ብር 139,647.81 ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ መሆኑ፤

ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 7 ተያይዟል)

4.1.2. <u>ሥጋት</u>

- ☞ የበጀት ዝውውር ሳይፈጸም ለየሒሳብ መደቦቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ክፍያ መፈጸም ተጠያቂነትን ሊስከትል ይችላል።

☞ የወጪ ሂሣብ በጀቱ በዕቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የኮሌጁን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል።

4.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ኮሌጁ የበጀት ዕጥረት ካጋጠመው በቅድሚያ የበጀት ሕጉን ተከትሎ የበጀት ዝውውር መጠየቅ ይኖርበታል። ከዚህም በተጨማሪ በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል።

4.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

በመደበኛ በጀት የተጠቀሱት ከተፈቀደው በጀት በላይ የተጠቀምነው አልባሳትና ህትመት ሲሆን ይህም ሊከሰት የቻለበት ዋናው ምክንያት ከሆስፒታሉ ስፋትና ሌሎች ቅርንጫፎችን እያስፋፋ በመሄዱ ለሁሉም ከህሙማን አልባሳት እስከ ባለሙያ ዩኒፎርም ድረስ የገበያ ዋጋውም ከፍተኛ ስለሆነብን በጀቱ በተለያየ ጊዜ ዝውውር ብናደርግም ሊበቃን ባለመቻሉ የተከሰተ ነው። በወራቤ ሆስፒታል ደግሞ የምግብ በጀት ባላቸው የአልጋ ቁጥር በተፈቀደው ተመን መሰረት ተጠይቆ የተሰራ ቢሆንም ሆስፒታሉ የምግብ አገልግሎት በ“Out Source” አውጥቶ በተዋዋለው መሰረት ሲሰራ የነበረ በመሆኑም በተራፊው በጀት ጨረታውን በድጋሚ እንዲወጣ ቢጠየቅም ጊዜ የወሰደባቸው በመሆኑ ተመላሽ የተደረገ ነው። በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት እናስተካክላለን።

4.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ሜዲካል ኮሌጁ የበጀት ዕጥረት ካጋጠመው በቅድሚያ የበጀት ሕጉን ተከትሎ የበጀት ዝውውር መጠየቅ ይኖርበታል። ከዚህም በተጨማሪ ሐገሪቷ ያላትን ውስን በጀት በማብቃቃት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ በተለይም በጎላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በቀሩት የሂሳብ ኮዶች ላይ በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። በተጨማሪም መሥሪያ ቤቱ የበጀት አጠቃቀሙ ላይ ክትትል

በማድረግ እና የማይጠቀምበትን በጀት ለይቶ በማውጣት የበጀት እጥረት ላለባቸው መስሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማሳወቅ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

5. ልዩ ልዩ

5.1. በቅጥርና በዕድገት ያልተሞሉ ክፍት የሥራ መደቦች፤

5.1.1. ግኝት

ኮሌጁ በዕቅድ የያዛቸውን ተግባራት በአግባቡ ለመፈጸም ይችል ዘንድ ክፍት የሥራ መደቦችን በሰው ኃይል መሙላት እንዳለበት ይታመናል። ነገር ግን ከሌጁ ከተፈቀደለት 2517 የስራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው 2032 ሲሆን 485 (19%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው ታውቋል።

5.1.2. ሥጋት

የተሟላ የሰው ኃይል ባለመኖሩ ምክንያት ኮሌጁ ዕቅዱን እንዳያሳካ ምክንያት ሊሆን እንዲሁም በአሰራር ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል።

5.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ኮሌጁ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ያስችለው ዘንድ ክፍት የስራ መደቦችን በቅጥርና በእድገት እንዲሞሉ ማድረግ ይኖርበታል።

5.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

የኮሌጁን ዕቅድ ለማሳካት ትልቁን ሚና የሚጫወተው በቂ የሰው ሀይል መኖሩ መሆኑን እንስማማለን። ነገር ግን ለኮሌጃችን ካስፈቀድናቸው የስራ መደብ ላይ ሙሉ ለሙሉ ለማመሟላት ከገጠሙን ችግሮች ውስጥ፦

- ✓ ከተፈቀደልን የስራ መደቦች ውስጥ ደረጃው ከፍ በማለቱ የሚጠይቀው የስራ ልምድ ከፍተኛ በመሆኑ በቅጥርም ሆነ በደረጃ እድገት ባለሙያ ልናገኝ ባለመቻሉ፣ (ለምሳሌ ዳታ ኢንኮደር የማህደር አከናዋኝ ፣ የህክምና ሬጅስተር…የመሳሰሉት)

- ✓ የተሰጠው ደረጃና ደመወዙ የተመጣጠነ ባለመሆኑ ለቅጥር ከገበያ ላይ ማግኘት ባለመቻሉ፣ (ለምሳሌ ሴክሬታሪ፣ ኦዲተር)
- ✓ በተጨማሪም "Out Source" ወይም በኤጀንሲ ይሸፈኑ የተባሉት የስራ መደቦች ነባር የሆኑትንም ወደ ሌላ ለማሸጋሸግ ችግር የገጠመን በመሆኑ፣ (ለምሳሌ ጥበቃ፣ ፅዳት ......የመሳሰሉት)

ቅጥር ለማከናወን ባለመቻሉ ነው።

በተረፈ የተሰጠውን አስተያየት ተቀብለናል። በአሁኑም ሰዓት በርካታ የስራ መደቦችን የደረጃ እድገትና ቅጥር በማውጣት እየሰራን መሆናችንን ለመግለጽ እንወዳለን። ያሉትን ክፍት ቦታዎች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እያሟላን እንገኛለን።

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በኮሌጁ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ስለተደረገለን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን።

አባሪ .1

<u>የተሰብሳቢ ሒሳብን የቆይታ ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር፤</u>

ተራ ቁጥር	የሂሳብ መደብ ቁጥር	የተሰብሳቢ ሂሳቡ ክፍያ የቆይታ ጊዜ	የቆይታው ጊዜ		ድምር
			ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመትድረስ የቆየ	ከአስር ዓመት በላይ የቆየ	
1.	4201	ከ1972 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ		13,774.33	13,774.33
2.	4211	ከሀምሌ 2008 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ	2,606,168.29		2,606,168.29
		ድምር	2,606,168.29	13,774.33	2,619,942.62

አባሪ .2

<u>መደበኛ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ (ክሬዲት ሚዛን) የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ዝርዝር፤</u>

ተራ ቁጥር	የተሰብሳቢ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር ካርድ ቁጥር	ክሬዲት ሚዘን የሚያሳዩ የተቀጽላ ሂሳቦች የሂሳብ መደብ ቁጥርና የገንዘቡ መጠን		ድምር
		4211	4253	
1.	0002	105.00		105.00
2.	0003	53.49		53.49
3.	0008	2,639.06		2,639.06
4.	0011	169.50		169.50
5.	0015	200.48		200.48
6.	0095	27.00		27.00
7.	0098	86.80		86.80
8.	0103	62.61		62.61
9.	0109	10.08		10.08
10.	0052	1,941.02		1,941.02
11.	0131	78.40		78.40
12.	0153	365.40		365.40
13.	0157	11,745.33		11,745.33
14.	0158	28.00		28.00
15.	0164	16,514.20		16,514.20
16.	0173	1,050.00		1,050.00
17.	0195	65.00		65.00
18.	0241	5,380.00		5,380.00
19.	0252	15,000.00		15,000.00
20.	0003		103,001.85	103,001.85
	ጠቅላላ ድምር	55,521.37	103,001.85	158,523.22

አባሪ. 3

<u>ከመመሪያ ወጪ ለሾፌሮች የተፈጸመ የውሎ አበል ክፍያ ዝርዝር፤</u>

ተራ ቁጥር	የሰራተኛው ስም	የተመደቡበት የሥራ መደብ	የተከፈለ የውሎ አበል	የተከፈለ ትርፍ ሰዓት	በመመሪያው መሰረት ለፈጸም የሚገባው የሾፌር ልዩ አበል	አለአግባብ ከመመሪያው ወጪ የተፈጸመ አበል
1	አቶ ተስፋዬ በላይነህ	የአስተዳደር ሰርቪስ		4,600.12	**3*600=1,800**	**2,800.12**
2	ዩናስ መንግስቱ	ፎረንሲክ ሜድስን የሰርቪስ አገልግሎት		8,563.57	**4*600=2,400**	**6,163.57**
3	ይታገሱ አቢ	ለፋይናንስና የሰው ሀብት ልማት የሰርቪስ አገልግሎት		4,029.95	**2*600=1,200**	**2,829.95**
4	ኤፍሬም መንግስቱ	ለአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሮቮስት የሰርቪስ አገልግሎት	**450.00**	2,211.01	**2*800=1,600**	**1,061.01**
5	ተስፋዬ ወዳጆ	ለምክትል ፕሮቮስት የሰርቪስ አገልግሎት		2,730.95	**2*800=1,600**	**1,130.95**
6	ተካልኝ እሸቱ	ፕሮቮስት የሰርቪስ አገልግሎት		1,931.83	**2*800=1,600**	**331.83**
7	ታሪኩ ኪዳኔ	ለፋይናንስና ግዥ የሰርቪስ አገልግሎት		5,123.97	**3*600=1,800**	**3,323.97**
8	ጥበቡ መንክር	ለለውጥ አመራር ዳይሬክተር የሰርቪስ አገልግሎት		4,453.87	**2*600=1,200**	**3,253.87**
9	ኢሳያስ ቸኮል	ለምግብ ማደራጃ የሰርቪስ አገልግሎት		3,268.28	**2*600=1,200**	**2,068.28**
10	ሲሳይ በላይ	የሰርቪስ አገልግሎት		4,050.28	**2*600=1,200**	**2,850.28**
11	ካሳሁን ሙሉታ	የሰርቪስ አገልግሎት	**450.00**	5,422.62	**4*800=2,400**	**3,472.62**
12	አሸብር አበበ	የሰርቪስ አገልግሎት		5,124.72	**3*600=1,800**	**3,324.72**
13	ነብዩ ተስፋዬ	ለላይዘን የአምቡላንስ አገልግሎት		2,059.52	**3*600=1,800**	**259.52**
		የሚዞር ድምር	**900.00**	**53,570.69**		**32,870.69**

ተራ ቁጥር	የሰራተኛው ስም	የተመደቡበት የሥራ መደብ	የተከፈለ የውሎ አበል	የተከፈለ ትርፍ ሰዓት	በመመሪያው መሰረት ለፈጸም የሚገባው የወራት ልዩ አበል	አለአግባብ ከመመሪያው ወጪ የተፈጸመ አበል
		የዞረ ድምር	**900.00**	**53,570.69**		**32,870.69**
14	ዳኛቸው ሙሉጌታ	ፕሮቦስት የሰርቪስ አገልግሎት	**1,800.00**	8,395.46	**4*800=3,200**	**6,995.46**
15	ጌታሁን ታደሰ	ለአቤት ሰራተኛ የሰርቨስ አገልግሎት		5,866.75	**4*600=2400**	**3,466.75**
16	ሰለሞን ሽፈራው	የሰርቪስ አገልግሎት	**450.00**	2,488.35	**2*800=1600**	**1,338.35**
17	መስፍን አየለ	የሰርቪስ አገልግሎት		5,138.00	**2*600=1200**	**3,938.00**
18	ዘላለም ልየው	የሰርቪስ አገልግሎት		2,954.40	**2*600=1200**	**1,754.40**
19	ዘሪሁን ወግራ	የሰርቪስ አገልግሎት		5,217.10	**2*600=1200**	**4,017.10**
20	ሚሊዮን ምትኩ	የሰርቪስ አገልግሎት		4,188.83	**2*600=1200**	**2,988.83**
21	ብርሃኑ ስንታየሁ	የሰርቪስ አገልግሎት		6,417.84	**2*600=1200**	**5,217.84**
22	ሰለሞን ተፈራ	የሰርቪስ አገልግሎት		3,602.70	**2*600=1200**	**2,402.70**
23	አብርሃም አበበ	የሰርቪስ አገልግሎት		2,104.22	**1*600= 600**	**1,504.22**
		ጠቅላላ ድምር	**3,150.00**	**99,944.34**	**36,600.00**	**66,494.34**

አባሪ. 4

<u>ለመኖሪያ ቤት ኪራይ የተፈጸመ ክፍያ ዝርዝር</u>፤

ተራ ቁጥር	ክፍያው የተፈጸመበት ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የወጪው ምክንያት	የውል ኮንትራት የሚቆይበት ጊዜ	ለክፍያው በቅድሚያ የተፈጸመ ወር ብዛት	የገንዘቡ ልክ
1	02/03/09	882782	ከወ/ሮ አበባ ገነቱ ጤናው ላይ የተፈጸመ ባለ ሁለት መኝታ አፓርትመንት ለአንድ አመት በብር አስር ሺህ ውል ተፈጽሞ የተከፈለ የቤት ኪራይ ፤	ለአንድ ዓመት	ለአንድ ዓመት	**120,000.00**
2	04/08/09	912795	ከአቶ እውነቱ ዳኛቸው ላይ ለአቤት ሆስፒታል ሥራ አስኪያጅ ለሆኑት ለአቶ ገሊላ መንግሥቱ መኖሪያ እንዲሆን ለሁለት ዓመት በብር አስር ሺህ ውል ተፈጽሞ የተከፈለ የቤት ኪራይ፤	ለሁለት ዓመት	ለስድስት ወር	**60,000.00**
3	04/08/09	912795	ከወ/ሮ ጽጌ በንቲ ላይ የአቤት ሆስፒታል የድንገተኛ የህሙማን ክፍል እና የህሙማን ፍሰት የህክምና ጥራት ዋና ክፍል ኃላፊ ለሆኑት ለዶ/ር አለኝታ ገ/እየሱስ መኖሪያ እንዲሆን ለሁለት ዓመት በብር አስራ ሶስት ሺህ ውል ተፈጽሞ የተፈጸመ የቤት ኪራይ ክፍያ፤	ለሁለት ዓመት	ለስድስት ወር	**60,000.00**
5	16/10/09	927667	ከወ/ሮ ዘቢባ ሽኩር ላይ የአቤት ሆስፒታል የፎረንሲክ ቶክሶኮሎጂ ምርመራዎች ባለሙያ ለሆኑት ለዶ/ር በጋሻው በላይ መኖሪያ እንዲሆን ለአንድ ዓመት በብር አስራ ሶስት ሺህ ውል ተፈጽሞ የተፈጸመ የቤት ኪራይ ክፍያ፤	ለአንድ ዓመት	የሶስት ወር	**30,000.00**
ድምር						**270,00.00**

አባሪ. 5

<u>በንብረት ወጪ ደረሰኝ ወጪ ተደርገው ያለሥራ በየቦታው የተቀመጡ ቋሚ ዕቃዎች ዝርዝር፤</u>

ተራ ቁጥር	ቀን	የሞ/22 ቁጥር	የዕቃው ዓይነት	ብዛት	የአንዱ ዋጋ	ጠቅላላ ዋጋ
1	26/10/2009	943595	Imported High Quality Chair	41	2,582.61	105,887.01
			Imported High Quality Low back Chair	486	2,100.87	1,021,022.82
			Gust Chair	108	2,404.35	259,669.80
			3 set metal chair	300	3,913.04	1,173,912.00
			Executive conference table	9	17,530.43	157,773.87
			Office table 160m	182	7,173.00	1,305,486.00
			Office table 180m	149	8,000.00	1,192,000.00
			Office table 2m	48	10,221.20	490,617.60
			Managerial High Back Chair	272	8,647.83	2,352,209.00
			High Quality Guest Chair	284	3,039.12	863,110.00
			High Quality Group table work station	150	13,909.56	2,086,434.00
			Imported High Quality with Drawer	100	2,581.60	258,261.00
			Gust Chair mask back for bag	87	2,404.35	209,178.45
2	26/10/2009	943596	Imported High Quality 3 set sofa	24	5,2130.43	1,251,130.32
			Group table work station	24	53555.65	1,285,335.60
			Imported High Quality Reception Chair	200	5,173.91	1,034,782.00
			Imported High Quality four door shelf	50	10,891.30	544,565.00
			Imported High Quality Gust Chair	59	2,582.61	152,373.99

ተራ ቁጥር	ቀን	የሞ/22 ቁጥር	የዕቃው ዓይነት	ብዛት	የአንዱ ዋጋ	ጠቅላላ ዋጋ
			High Quality Conference Table	2	96,913.04	193,826.00
			Imported High Quality 5 set sofa	6	52,130.43	312,782.58
			Office Sofa High Quality single	50	1,2130.43	606,521.50
			Group Table work station	6	53,555.65	321,330.90
			Group computer work station	17	55,000.00	935,000.00
			Imported High Quality Shelf two glass	297	5,669.57	1,683,862.00
			Three door shelf with glass	100	8,019.13	801,913.00
3	26/10/2009	943597	Reception table with drawer to table	2	30,134.78	60,269.56
			High Quality Imported Oval shape	1	15,000.00	15,000.00
			ድምር			20,674,254.00

አባሪ. 6

<u>በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ ሂሳቦች ዝርዝር፤</u>

ተራ ቁጥር	ቀን	የወጪ ቫውቸር ቁጥር	ገንዘቡን የተቀበለው ሰው ሥም	የሂሣብ ኮድ ቁጥር	የወጪው ምክንያት	የገንዘቡ ልክ
1.	30/12/08	BPV 0833623	ወ/ሮ መስታወት በቀለ	6231	ወደ ኬኒያ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	41,426.50
2.	30/12/08	BPV 0833624	ወ/ሮ ኑኑ ወልዴ	6231	ወደ ኬኒያ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	41,426.50
3.	30/12/08	BPV 0833625	ወ/ሮ ሮማን ኃ/ማርያም	6231	ወደ ኬኒያ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	41,426.50
4.	30/12/08	BPV 0833626	አቶ ታደሰ ሳህሌ	6231	ወደ ኬኒያ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	41,426.50
5.	30/12/08	BPV 0833627	አቶ ሃብታሙ ዘውዴ	6231	ወደ ኬኒያ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	41,426.50
6.	30/12/08	BPV 0833628	ወ/ሮ ገነት አዱኛ	6231	ወደ ኬኒያ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	41,426.50
7.	30/12/08	BPV 0833630	ዶ/ር አድሃኖም ግርማይ	6231	ወደ ኬኒያ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	41,426.50
8.	30/12/08	BPV 0833629	ወ/ት እሴተ ሸዋ	6231	ወደ ኬኒያ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	41,426.50
9.	30/12/08	BPV 0858174	ዶ/ር ቤዛዬ አበበ	6231	ወደ ህንድ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	95,978.03
10.	30/12/08	BPV 0858173	ዶ/ር የምስራች መኮንን	6231	ወደ ህንድ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	95,978.03
11.	30/03/09	BPV 911377	ወ/ሮ ነጻነት ተካልኝ	6231	ወደ ህንድ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	9,567.77
12.	30/03/09	BPV 911359	ዶ/ር ሄና አበራ	6231	ወደ ግብጽ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	18,006.26
13.	30/03/09	BPV 911360	ዶ/ር የምስራች ጫኔ	6231	ወደ ግብጽ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	18,006.26
14.	30/03/09	BPV 911361	ዶ/ር ገዳ ሊሊሳ	6231	ወደ ግብጽ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	18,006.26
15.	30/04/09	JV 90913	ወ/ሮ ነጻነት ተካልኝ	6231	ወደ ህንድ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	35,831.25
16.	30/05/09	BPV 911380	ሚ/ር ኑዛታ ዓለም	6231	ወደ ህንድ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	8,107.58
17.	30/05/09	JV 90915	ሚ/ር ኑዛታ ዓለም	6231	ወደ ህንድ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	30,348.00
18.	30/08/09	BPV 927054	ሲስተር ብሩክታዊት ዳኘው	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
19.	30/08/09	BPV 927055	ነርስ አለኸን ቀረብኝ	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
20.	30/08/09	BPV 927056	ለነርስ ሣምሶን ታረቀኝ	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
21.	30/08/09	BPV 927057	ሲስተር አዚንያ አ/ቃድር	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
22.	30/08/09	BPV 927058	ሲሰተር ገነት ሽፈራው	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
23.	30/08/09	BPV 927059	ፀሐይ አይተነው	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
24.	30/08/09	BPV 927060	ሲስተር ነጃት ከማል	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
25.	30/08/09	BPV 927061	ሲሰተርአይናለም ገብሬ	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
26.	30/08/09	BPV 927062	ሲሰተርአይናለም ገብሬ	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
27.	30/08/09	BPV 927063	ሲስተር ፍቅርተ እሸቱ	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
28.	30/08/09	BPV 927064	ነርስ ዘላለም ፍቃዱ	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
			የሚዞር ድምር			1,038,308.02

ተራ ቁጥር	ቀን	የወጪ ቫውቸር ቁጥር	ገንዘቡን የተቀበለው ሰው ሥም	የሂሣብ ኮድ ቁጥር	የወጪው ምክንያት	የገንዘቡ ልክ
29.			የዞረ ድምር			1,038,308.02
30.	30/08/09	BPV 927065	ዶ/ር ቶላ ባይሳ	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
31.	30/08/09	BPV 927066	ሲስተር ጺዮን አድማሱ	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
32.	30/08/09	BPV 927067	ሲስተር ንግሥት ትዕዛዙ	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
33.	30/08/09	BPV 927068	ነርስ ልዋየሁ አለማየሁ	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
34.	30/08/09	BPV 927069	ነርስ ምስጋና ታምሩ	6231	ወደ ናይሮቢ ለሥልጠና ሲሄዱ የተከፈለ አበል	34,278.78
						1,209,701.92

<u>ከ10% በላይ ያልተሰራበት በጀትና ለየሂሳብ ኮዶቹ</u>

<u>ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ ሂሳብ ዝርዝር፤</u>

የወጪ ሒሳብ መደብ	የተፈቀደ በጀት	በሥራ ላይ የዋለ በጀት	ያልተሰራበት በጀት		ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ	
			የገንዘቡ መጠን	በፐርሰንት (%)	የገንዘቡ መጠን	በፐርሰንት (%)
I. የመደበኛ በጀት						
የበጀት ኮድ 346 -01- 01						
6133	416,880.81	330,740.61	86,140.20	21		
6213	9,200,000.00	9,229,497.63			29,497.63	**0.32**
6257	2,000,000.00	1,758,851.90	241,148.10	12		
የበጀት ኮድ 346-02 -01						
6211	5,260,128.00	5,309,794.76			49,666.76	0.94
6213	1,200,000.00	1,780,073.64			580,073.64	48
የበጀት ኮድ 346-03-01						
6211	3,000,000.00	3,179,692.50			179,692.50	6
6133	459,424.68	374,346.72	85,077.96	19		
የበጀት ኮድ 346- 02-02						
6113	2,160,344.00	2,167,020.10			6,676.10	0.31
6131	1,645,000.00	1,858,271.60			213,271.60	13
6133	200,009.93		200,009.93	100		
6214	10,000,000.00	10,071,760.27			71,760.27	0.78
6216	3,784,320.00	877,358.47	2,906,961.53	77		
6217	800,000.00	1,176,931.07			376,931.07	47
6231	1,580,000.00	1,614,152.09			34,152.09	2
6232	80,000.00	9,544.00	70,456.00	88		
6252	70,000.00	47,620.00	22,380.00	32		
6256	200,000.00	158,417.90	41,582.10	21		
6259	150,000.00	152,376.26			2,376.26	2
ድምር	42,206,107.42	40,096,449.52	3,653,755.82		1,544,097.92	
II. የካፒታል በጀት						
የበጀት ኮድ 346-02- 01- 00 -002						
6321	1,019,650.00	1,159,297.81			139,647.81	14
ጠቅላላ ድምር	**43,225,757.42**	**41,255,747.33**	**3,653,755.82**		**1,683,745.73**	

በሥራ አመራር ሪፖርት በተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር

የኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤት ስም:- ____________________________

ኦዲት የተደረገው ሂሳብ በጀት ዓመት:- ____________________________

የተዘጋጀበት ቀን:- ___________________

ተራ ቁጥር	የኦዲት ግኝቶች	የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች	እስከአሁን የተወሰዱ ማስተካከያ እርምጃዎች	ቀሪ ማሻሻያ ሃሳቦች ተግባራዊ የሚደረጉበት ጊዜ	ኃላፊነት የተሰጠው የሥራ ክፍል	ምርመራ

ማሳሰቢያ:- ይህ መርዓ-ግብር እና የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤትዎ እንደደረሰ የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ ተሞልቶ በ7 ቀናት ውስጥ ለመ/ቤታችን ካልተመለሰ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በምናቀርበው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ "ለኦዲት ሪፖርት ማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር መልስ ያልላኩ መሥሪያ ቤቶች" ዝርዝር ውስጥ እና እርምጃ አለመወሰዱ ተጠቅሶ ለምክር ቤቱ ሪፖርት የሚቀርብ መሆኑን እንገልፃለን።